# ይድረስ፡ለኢትዮጵያ፡ሕዝብ፤

“ኢትዮጵያ፡ሀገሬ፡ሞኝ፡ነሽ፡ተላላ፣
የሞተልሽ፡ቀርቶ፡የገድደለሽ፡በልላ”።

ብለው፡ቀኝ፡ጌታ፡ዮፍታሔ፡ንጉሤ፡እንደ፡ገለጹት፡ዛሬም፡ለፈጣሪህ፡በይፋ፡እግዚአታን፡የተከለከልከው፡በሐቀኛው፡ሥውር፡እግዚአታህ፡በእውነት፡እንደምታሸንፍ፡አንጠራጠርም።

አመፀኛው፡ፋሽስት፡ለገሠ፡ዜናዊና፡ዓዜብ፡ከሌሎች፡ግብረ፡አበሮች፦ስብሀት፡ነጋ፣በረከት፡ስምዖንና፡የቀሩትም፡እነ፡ሆድ፡አምላኩ፡ጓደኞች፡ለኢትዮጵያ፡ልማት፡ተብሎ፡በዓለም፡ባንክ፡ከተሰጠው፡ብድርና፡ለጋሽ፡መንግሥታትም፡ከሰጡት፡የዕርዳታ፡ገንዘብ፡ሃምሣ፡በመቶው፡በእነዚህ፡ዘራፊዎች፡ስም፡ስዊስ፣ማሌዚያና፡በመሳሰሉት፡አገሮች፡ሥውር፡አደራ፡አስቀማጭ፡ባንክ፡ውስጥ፡ያኖሩት፡ወሰን፡የሌለው፡ገንዘብ፡አልለ።እንዲሁም፡በሌላ፡አገር፡ያልተደረገ፡የሕዝብ፡ሀብት፡የሆነውን፡የአዶላና፡መሰል፡ቦታ፡የሚገኜውን፡የወርቅ፡ሀብት፡የአመፀኛው፡ለገሠ፡ዜናዊ፡ሸሪክ፡መሐመድ፡አላሙዲ፡እያስጠፈጠፈ፡መውሰዱ፡ተገቢ፡ነወይ?።ስለዚህም፡ፋሽስቱ፡አምባገነን፡ለገሠ፡ዜናዊና፡ግብረ፡አበሮቹ፡ቀኑ፡ሲደርስ፡የሚጠየቁበት፡መሆናቸውን፡አሳውቃቸው።በምክር፡ቤቱ:ውስጥ፡የተቀመጡት፡ግብስብስ፡አማካሪዎች፡ከሕዝቡ፡የተቀበሉትን፡አደራ፡የማይፈጽሙ፡ከሃዲዎች፡ዝምም፡ብለው፡እጃቸውን፡እያነሡ፡ሆዳቸውን፡ይሞላሉ፡እንጂ፣የአገሪቱ፡ጉዳይ፡አይቆረቁራቸውም።ሌላዋ፡ጨካኝ፡ዘራፊ፡ዓዜብ፡መስፍን፡በማናቸውም፡የንግድ፡ዘርፍ፡ተካፋይ፡ስትሆን፣አልፋ፡ተርፋ፡ያገለገሉ፡መኪናዎችን፡አስመጭ፡በመሆን፡የምታካብተውን፡ገንዘብ፡በዝምምታ፡ያለኸው፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡በትዕግሥት፡ትመለከተዋለህ።ዛሬ፡በግዜያቸው፡ይጨፍሩበት።ነገ፡ዋጋቸውን፡ያገኙታል።ምንም፡እንኳ፡ለግዜው፡በአግዐዝያን፡ድልብና፡ዱዳ፡ወታደሮቻቸው፡እያስፈራሩ፣ኢትዮጵያ፡ቀደም፡ያፈራቻቸው፡ብቃት፡ያልላቸው፡አመዛዛኝና፡ገለልተኛ፡ዳኞች፡ቀርተው፡በጎጥ፡ልዩነት፡ሕዝብን፡እያሰቃዩ፡በፍርድ፡ሳይሆን፡በአረመኔው፡አመፀኛ፡ለገሠ፡ዜናዊ፡ውሳኔ፡ሕዝብ፡እየገደሉ፣በእሥር፡ቤት፡እያሰቃዩ፡ለመኖር፡ቢወስኑም፤ትዕግሥትህ፡ያልለቀ፡ዕለት፡ወዮላቸው!!።በዓለማት፡የሚደረገውን፡እንቅስቃሴ፡እየው።ቱኒዚያን፣ግብፅን፣ሊቢያን፡ሶርያን፣ባሕሬንና፡ጐረቤት፡የመን፡ዛሬ፡የሚገኙበትን፡ሁኔታ፡ትምህርት፡ይሁናቸው።“በሰፈሩት፡ቁና፡መስሰፈር፡አይቀርም”።የሚገርመው፡ነገር፡ቢኖር፡በኢትዮጵያ፡ጐረቤት፡አገሮችንና፡በመከከለኛው፡ምሥራቅ፡የተነሣውን፡የሕዝብ፡እንቅናቄ፡ተመልክተው፡ነገ፡ኢትዮጵያም፡አይደርስም፡በማለት፡“ረሀብና፡ችግርን”፡የፈሊጥ፡(የፖለቲካ)፡መሣሪያ፡በማድረግ፡ላይ፡መሆናቸው፡ነው።የታሪክ፡ባለቤት፡በሆንከውም፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ላይ፡መጫወት፡ለአረመኔ፡ነፍሰ፡ገዳዮች፡ለገሠ፡ዜናዊና፡ለእነ፡በረከት፡ስምዖን፡ዛሬ፡ደስታቸው፡ነገ፡ኀዘናቸው፡ይሆናል።በጸጥታ፡ሰዎች፡ተንከባክበው፡እነ፡ፋሽስቱ፡ለገሠ፡ዜናዊ፡እንደሚያደርጉት፡ሁልሉ፤በአስተዳደር፡ብልግና፡ይሠሩ፡የነበሩት፦ሙባረክ፣ጋዳፊ፣ሀሳድና፡የየመኑ፡መሪ፡ዛሬ፡በምን፡ሁኔታ፡ላይ፡ናቸው?።ብለው፡እንዴት፡አያስቡም?።አንተን፡የትኢዮጵያን፡ሕዝብ፡ከመናቅ፡የመነጨ፡ሳይሆን፡ይቀራል?።ሰሞኑን፡ሙባረክ፡ባደረገው፡የአስተዳደር፡በደል፡በቃሬዛ፡ተወስዶ፡ፍርድ፡ቤት፡እየቀረበ፡ቅጣቱን፡ሲጠብብቅ፡ይታያል።ታዲያ፡ይኸን፡ማየቱ፡ለአመፀኛው፡ለገሠ፡ዜናዊ፣ለዓዜብ፡መስፍን፣ለበረከት፡ስምዖንና፡ለቀሩትም፡አመፀኞች፡ትምህርት፡ሆኗቸው፡አንተን፡የኢትዮጵያን፡ሕዝብ፡ከማሰቃየት፡እንዲቆጥጠቡ፡ምን፡ልትላቸው፡ይገባል?።ካልሆነ፡ግን፡ወዮልላቸው!!።የኃያሉ፡እግዚአብሔርን፡ቁጥጣ፡ሊቋቋሙት፡አይችሉምና!!!።

የትግሬ፡ወያኔው፡(አመፀኛው)፡አስተዳደር፡መሪ፡ፋሽስቱ፡ለገሠ፡ዜናዊ፡ልማት፡አድርጌ፡አልለሁ፡እያለ፡የማታለያ፡ወሬውን፡ይነዛል።በክልልሉ፡ያደልለባቸው፡የትግሬ፡አግዐዚ፡ወታደ

ሮቹን፡የእርሱ፡ጠብባቂ፡አድርጐ፤ሌሎች፡የኢትዮጵያ፡ወታደሮች፡አገር፡ውስጥ፡በማገልገል፡ፈንታ፡ኪሱን፡ለማዳበር፡ሲል፡ሰላምን፡ስለማይወድ፡ገንዘብ፡መለምመኛ፡አድርጓቸው፡በሱማሊያ፡ግንባር፡በመዋደቅ፡ላይ፡ናቸው።በቅርቡ፡ደግሞ፣በሰላም፡አስጠብባቂ፡ስም፡በደቡብ፡ሱዳን፡ልኮ፡ለግልል፡ጥቅሙ፡ማወፈሪያ፡አድርጐ፡አስገድሏቸዋልና፡ለትውልድድ፡ታሪክ፡የማይርረሳ፡ይሆናል።በጣም፡ከሚዘገንነውም፡ነገር፡በእርሱ፡ዘሮች፡ዓይነ፡ቁራኛ፡እያስጠብበቀ፡የፊት፡ቀዳሚ፡ተዋጊ፡እያደረገ፡በሥጋት፡ማሸማቀቁ፡ነው።ኤሌክትሪክ፣ውሃ፣ስኳርና፡ዘይት፡በፈረቃ፡እንዲዳርረስ፡እያደርረገ፤በሌላ፡በኩል፡ኤሌክትሪክ፡ለሱዳንና፡ለጅቡቲ፡እየሸጠ፡ገቢውን፡ለሀገር፡አገልግሎት፡ሳይሆን፡ለራሱ፡ወደ፡ግልል፡ሳጥኑ፡ያስገብባል።አዳዳስ፡ሕንፃዎች፣ቀጥተኛና፡የቀለበት፡መንገዶች፡ተሠርተዋ፡እንበል።ዕቅዱ፡ዛሬ፡ሳይሆን፡ቀደም፡ብሎ፡የተዘጋጀ፡ስለ፡ነበበረ፡እንደ፡አዲስ፡ነገር፡ማውራቱ፡ሕዝብን፡ለማታለል፡የተደረገ፡ወሬ፡ነው።ይህም፡ቢሆን፡የአገርን፡ክብርና፡ነፃነት፡አናስደፍርም።ለማንም፡የውጭ፡መንግሥታት፡ሥውር፡ደባ፡አናንበድድም።ተገዥም፡አንሆንም።ይል፡የነበረው፡የኢትዮጵያ፡መንግሥት፡የዓለም፡ባንክ፡ብድር፡በመከልከሉ፡ነበረ።ዛሬ፡እንደሚጐርፈውና፡ከመንግሥታትም፡ዕርዳታ፡ባለማግኘቱ፡ሥራው፡ተጓድሏል።አሁን፡ግን፡አጎብዳጅና፡የአሽከርነት፡ጠባይ፡የተዋሃደውና፡ኢትዮጵያን፡ከሀዲው፡ለገሠ፡ዜናዊ፡ኪሱን፡ለማወፈር፡ሲል፤የአገሪቱን፡ክብርና፡ነፃነት፡አስረግጦ፡በግራና፡ቀኝ፡የባንክ፡ብድሩም፡ሆነ፡የዕርዳታው፡ገንዘብ፡ስለጎረፈለትም፡እየፈረሰ፡ያልለውን፡የቀለበት፡መንገድ፡ሆነ፡በከተማውም፡ውስጥ፡ለውስጥ፡መንገዶች፡ሊሠሩ፡ተችሏል።ለመንገድ፡ሥራ፡ማልሚያ፡ከተሰጠው፡ገንዘብ፡ሃምሣ፡በመቶው፡ማሌዚያና፡ስዊስ፡ባንክ፡በዘራፊው፡ፋሽስት፡ለገሠ፡ዜናዊና፡በአበሮቹ፡ስም፡ተቀምጧል።ፋሽስቱ፡ለገሠ፡ዜናዊ፡አሁን፡እርሱ፡የሚያስተዳድረውን፡በእውነተኛነት፡ለሕዝቡ፡ካማሳወቅ፡ይልቅ፣የቀድሞዎችን፡ወቀሳ፡ስለሚቀናውና፡የሕዝብ፡ቅስም፡በሚሰብር፡ስድብ፡ስለሚናገር፡ሳንወድ፡በግድ፡ከቀድሞው፡መንግሥት፡ትንሽ፡እንተንፍስ።የአመፀኛው፡ለገሠ፡ዜናዊ፡አገር፡አስተዳደር፡ለትውልድ፡የሚተላለፍ፡ዕዳ፡ሲተው፤ታሪክ፡የሚያስታውሰው፡ከአርባ፡ዓመት፡በፊት፡የነበሩት፡መሪ፡አፄ፡ኃይለ፡ሥላሴ፡ግን፡የአገሪቱን፡ችግር፡በራሷ፡በአገሪቱ፡ሃብት፡መቋቋምና፡ግዜ፡ሲፈቅድ፡ለማልማትና፡አገሪቱን፡ከዕዳ፡ነፃ፡በማድረግ፡መጪውም፡ትውልድ፡ጥሮ፡ግሮ፡አገሪቱን፡ያለዕዳ፡እንዲያለማ፡የሚያስቡ፡መሪ፡እንደ፡ነበሩ፡ታሪክ፡ይናገራል።ዛሬ፡ግን፡የትግሬ፡ወያኔው፡አረመኔ፡ለገሠ፡ዜናዊና፡ግብረ፡አብበሮቹ፡ኪሳቸውን፡ለማወፈር፡ይህን፡የመሰለው፡ተግባር፡በሕሊናቸው፡አይታሰብም።ስለዚህ፣የልማቱን፡ነገር፡ሆድ፡ይፍጀውና፡እንደ፡ተከደነ፡ለታሪክ፡ይቆይ።

“ዘር፡ከልጓም፡ይስባል”፡እንደሚሉት፡አመፀኛው፡ፋሽስት፡ለገሠ፡ዜናዊ፡በቅርቡ፡የራሱን፡ጋዜጠኛ፡መስከረም፡ጌታቸው፡የምትባል፡አዘጋጅቶ፡ጀግኖች፡መይሣው፡ካሣ፡አፄ፡ቴዎድሮስንና፡እምዬ፡አፄ፡ምኒልክን፡በማንቋሸሽ፡የተናገረውን፡በዓለም፡አቀፉ፡ጎዋ፡ዓውታር፡ተመልክተናል።እነዚህ፡እንከን፡የልለሽ፡አፄዎችና፡ብርቱ፡መሪዎቻችን፡የኢትዮጵያን፡አንድነት፡መሥራች፡አባትና፡አስፈጻሚ፡ልጅ፡ሆነው፡ያቆዩን፡ለመሆናቸው፡ታሪክ፡ይመሰክራል።ስለ፡አፄ፡ዮሐንስ፡ግን፡የተነፈሰው፡የልለም።ምናልባትም፡የተንኮሉ፡ምንጭ፡እርሳቸው፡ስለ፡ነበሩ፡አስተባብሎ፡ለመናገር፡ተቸግሯል፡ወይም፡ዝምምታን፡መርጧል።ኢትዮጵያዊው፡ጀግና፡ራስ፡አሉላ፡እንግዳ፡የባሕረ፡ምድር፡ገዥ፡ሆነው፡አሥመራ፡በመኖር፡የኢትዮጵያን፡ወደብም፡በማስከበር፡ተወድደው፣በጠላት፡ተፈርተውና፡ተከብረው፡ሲሠሩ፡አፄ፡ዮሐንስ፡ቀንተው፡ወይም፡ሥልጣኔን፡ይቀናቀነኛል፡በሚል፡ፍራቻ፡ከገዥነታቸው፡በማንሣታቸው፡ነበረ፡በክፍት፡በር፡ጠላት፡ገብቶ፡ኢትዮጵያን፡ሊወርና፡አፄ፡ቴዎድሮስም፡በአፄ፡ዮሐንስ፡መንገድ፡መሪነት፡እንግሊዞች፡መቅደላ፡ገብተው፡ሲዋጉ፡እራሳቸውን፡ያጠፉት።እናም፣አፄ፡ዮሐንስ፡እንኳን፡በሕይወታቸው፡ሞተውም፡ተወዳጅነት፡የሌላቸው፡ጨካኝ፡ሰው፡ነበሩ።ለዚህም፡ማስረጃ፡አንዷን፡መዘን፡እንሆ!።-“አፄ፡ዮሀንስ፡መተማ፡በጦርነቱ፡ውስጥ፡መሞታቸው፡ሲሰማ፤ንጉስ፡ተክለሃይማኖት፡አጎበር፡ያስተክሉና፡እዚያ፡ውስጥ፡የንጉሱን፡ምስል፡ያስቀምጡና፡የጎጃምን፡ህዝብ፡“ክተት”፡ብለው፡እንዲያለቅስ፡ያዝዙታል።ከዚያ፡......አንድ፡

አስለቃሽ፡ትመጣና፡-

“ሲገዚ፡እንዳልኖሩ፡እንዳልበሉ፡ሁላ፣
ለተባይ፡ሰጥተውን፡ዳርገውን፡ለተኩላ፣
ወጥተው፡ሲቀመጡ፡ንጉሱ፡ጅበላ፣
በጃችን፡ሳይጠጣ፡በጃችን፡ሳይበላ፣
ደም፡መላሽ፡ሆነን፡መሀመድ፡አብደላ፣
ዘሩን፡ይባርክለት፡እሚያምንበት፡አላ”።

ስትል፡ንጉሱ፡ተበሳጭተው፡እንድትያዝ፡ያደርጉና፡ልቅሶው፡እንዲቀጥል፡ያዝዛሉ። ከዚያም፡ሁለተኛይቱ፡አስለቃሽ፡ትነሳና፡-

“ደህና፡ተሰናድቶዋል፡ተጠርጓል፡መንገዱ፣
አጼ፡በሄዱበት፡ንጉሱም፡ይሂዱ!”።

ስትል፡ለልቅሶ፡የከተተው፡ህዝብ፡በማልቀስ፡ፈንታ፡በሳቅ፡ያወካል።ያን፡ጊዜ፡ንጉሱ፡የሚያደርጉትን፡አጥተው፡“የተያዘችውን፡አስለቃሽ፡ልቀቁ”፡ብለው፡ልቅሶውን፡ፈትተው፡ተነሱ፡ይባላል”።

[*፩] የእልም፡እዣት፤በሊቀ፡ምሁር፡ሐዲስ፡ዓለማዬሁ።ገጽ፡፳፱፻፩።

ታዲያ፡ሕዝብ፡ሐሣቡን፡የመግለጽ፡ነፃነት፡(ዴሞክራሲ)፡በዚያን፡ዘመን፡ኢትዮጵያ፡አልነበራትም፡ማለት፡ይቻላል?።እናም፣በእኛ፡ምርምር፡የሕዝብን፡ልቅሶና፡እግዚዎታ፡የፋሽስቱ፡ለገሠ፡ዜናዊ፡አስተዳደር፡የከለከለው፡ለበቀል፡ነው፡ብለን፡እናሥባለን።ለምን፡ቢባል፣አፄ፡ዮሐንስ፡ለሥልጣና፡ዝና፡ሲሉ፡በጨካኝነታቸውና፡ሥር፡በሰደደ፡የዘረኝነት፡ጥላቻቸው፡ተረግመዋላ!!። ለዚህ፣ከሃዲው፡ፋሽስት፡ለገሠ፡ዜናዊም፡ሁለቱ፡ንጉሠ፡ነገሥታት፡ደክመው፡የገነቡትን፡አንድነት፡ጠልቶ፤ኢትዮጵያ፡ፈርሳ፡መስሠራት፡አልለብባት፡በሚል፡አጋንታዊ፡ዕቅዱ፡ትግሬን፡እየገነባ፡የቀድሞውን፡አገዛዝ፡ሥርዓት፡ከመይሣው፡ካሣ፡አፄ፡ቴዎድሮስ፡ቀደም፡ብሎ፡ወደ፡ነበረው፡ዘመነ፡መሳፍንት፡ሥርዓት፡መልሶ፡አዲስ፡ታሪክ፡ሠሪ፡መስሏል።እምዬ፡አፄ፡ምኒልክ፡ያቋቋሙት፡የመጀመሪያውን፡መብራት፡ኃይልም፡ለፈንሣይ፡ሸጦ፡የመይሣው፡ካሣ፡አፄ፡ቴዎድሮስንና፡የእምዬ፡አፄ፡ምኒልክን፡መሠረት፡በማጥፋት፡ላይ፡ስለ፡ሆነ፡ፍርዱን፡ለአንተው፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡መተው፡ይሆናል።በእምዬ፡አፄ፡ምኒልክ፡ታሪክ፡ዝነኛ፡መሆን፡ቅናትና፡ጥላቻ፡በተለይ፡የሸዋ፡አማራ፡ብሎ፡የዘረኛነት፡ዐዋጁን፡አስሰምቶ፡እንሆ!፡እስታሁን፡ነፍጠኛ፣ጨለምተኛ፣ትምክህተኛ፣...........የመሳሰሉትን፡ቃላት፡እየደረደረ፡ይጮሀል።በመይሳው፡ካሣ፡አፄ፡ቴዎድሮስም፡ታሪክ፡ዝነኛ፡መሆን፡ቅናትና፡ጥላቻ፡አጽማቸው፡የተቀበረበትን፡ገዳማዊ፡ቦታ፡ለሱዳን፡ሸልሟልና፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ልታስብበት፡ይገብባል።

በአፄ፡ኃይለ፡ሥላሴ፡ዘመነ፡መንግሥት፡የኢትዮጵያ፡ግዛት፡ወሰኗ፡ሳይደፈርና፡አንድነቷ፡ተጠብቆ፡ከዛሬ፡፵፰፡ዓመታት፡በፊት፡የነበረው፡ትውልድ፡ተባብሮና፡ተፋቅሮ፡በመማር፡እዬሠራ፡ይኖር፡እንደ፡ነበረ፡ሁላችንም፡በታሪክ፡እናውቀዋለን።ከዚያ፡ወዲህ፡የተገኘው፡ትውልድማ፡በሦስት፡ፈረቃ፡ትምህርቱን፡የተከታተለ፤የአገሩን፡ታሪክ፣ግብረ፡ገብና፡የሀገር፡ፍቅርን፡ያልተረዳ፡ግራ፡የገብባው፡ከንቱ፡ትውልድ፡በመሆኑ፡ዛሬ፡አገሪቱ፡ያለችበት፡ሁኔታ፡በቂ፡ማስረጃ፡ነው።በዚያን፡ጊዜ፡የአገር፡አገዛዝ፡ችግር፡ነበረ፡ብንል፣የመሬት፡ድልድል፡አለመፈጸም፣የፍርድ፡ቤቶች፡ጉዳይና፡የመሳሰሉት፡ነበሩ።የእነዚህንም፡ቢሆን፡ማሻሻል፡ይገባል፡እንጂ፡ለማፈራረስ፡ታጥቆ፡በመነሣት፡የጎሣ፡ፈሊጥ፡(ፖለትካ)፡መሥርቶ፡ኢትዮጵያ፡ተበታትና፡ሩዋንዳና፡ብሩንዲ፡እንደ፡ደረሰው፡የደም፡ባሕር፡እንድትሆን፡በፋሽስቱ፡ለገሠ፡ዜናዊ፡ዕቅድ፡የሚያስወጣ፡አልነበረም።ተማሪዎችም፡በአፄው፡ዘመን፡ችግሩ፡እንዲወገድ፡“መሬት፡ለአራሹ”፡መፈክርን፡አንግበው፡የተነሡበትም፡ዓላማ፡ሰላማዊ፡ሰልፍ፡አድርገው፡በነበረበት፡ወቅት፡በውሃና፡አስለቃሽ፡ጢስ፡ያባርሯቸው፡ነበረ፡እንጂ፣እንደ፡ዛሬው፡በጥይት፡ይገድደሉ፡አልነበረም።ከሰላማዊ፡ሰልፈኞችም፡መካከል፡ወደ፡የሕግ፡ዘበ

ኛ፡(ፖሊስ)፡ጣቢያ፡ተወስደው፡ምንም፡ነገር፡ሳይነካቸው፡በቁም፡እሥር፡ባቆዩዋቸው፡ግዜ፡አባቶቻቸው፡ንጉሡ፡ፊት፡ቀርበው፡ለልጆቻቸው፡ይቅርታ፡እንዲደረግላቸው፡ሲጠይቁ፡-“እናንተ፡በሥጋ፡ብትወልዷቸው፡ለእኛም፡የመንፈስ፡ልጆቻችን፡ስለ፡ሆኑ፡ይቅርታ፡አድርገንላቸዋልና፡ወደ፡የትምህርት፡ገበታቸው፡ይመለሱ።እናንተም፡ምከሯቸው”።የሚል፡መልስ፡ሰጥተው፡አሰናበቷቸው።ሲሉ፡አንድ፡ስማቸው፡እንዳይጠቀስ፡ያስታወቁን፡የቀድሞ፡እንደራሴ፡(አምባሳደር)፡ነግረ ውናል።አረመኔው፡አመፀኛ፡ለገሠ፡ዜናዊና፡ግብረ፡አበሮቹም፡በዚያ፡ዓይነት፡በጢስ፡ማልቀስና፡ውሃ፡መርረጨት፡ነበሩበትና፡ዛሬ፡ሥልጣኑን፡ሲይዙት፡ፈርተው፡በጥይት፡መደብደብን፡መረጡ።ለሥልጣንና፡ዝና፡ሲሉ፡ሥር፡የሰደደ፡አክራሪ፡የዘር፡ጥላቻቸውን፡የወረሱት፡ከከሃዲ፡ወላጆቻቸው፡በመሆኑ፡አጠራጣሪ፡እንደማይሆን፡ማስረጃው፡ከፋፍሎ፡ለመግዛት፡እንዲመቸው፡ሙሶሎኒ፡ያዘዘጋጀውን፡ቢጋር፡በመጠቀም፡የሚያከናውኑትን፡ስለምናየው፡ነው።

ባሕረ፡ምድርን፡(ኤርትራን)፡ተደርጐ፡በማይታወቅ፡ሁኔታ፡ግራና፡ቀኙ፡ሕዝብ፡ድምፁን፡ሳይሰጥበት፡የዘላለም፡ምኞቱ፡ለነብበረው፡የግብፅ፡የውጭ፡ጉዳይ፡ምሉክ፡(ሚኒስትር)፡በዚያን፡ወቅት፡የተባበሩት፡መንግሥታት፡ዋና፡ጸሐፊ፡ለቡጥሮስ፡ጋሊ፡አረመኔው፡ለገሠ፡ዜናዊ፡ደብዳቤ፡ጽፎ፡እንድትገነጠል፡ሲያደርግ፡ኢትዮጵያን፡ያለ፡ባሕር፡በር፡አስቀርቷታል።ኢሣያስ፡አፈወርቅንም፡ለማባረር፡ተመቸው።ቆይቶም፡በሁለቱ፡ወገኖች፡መካከል፡በዛለአንበሣና፡በበአዴን፡ጦርነት፡ጊዜ፡የኢትዮጵያ፡ወታደሮች፡በአሸናፊነት፡አሰብን፡ለመያዝ፡፲፰፡ኪሎ፡ሜትር፡ሲቀራቸው፡ሠራዊቱ፡ወደ፡ፊት፡መገስገሱን፡እንዲያቆም፡አደረገ።ዛሬ፡የአሰብን፡በር፡ለአክስቱ፡ልጅ፡ለኢሣያስ፡አፈወርቅ፡አደረገና፡አንደላቀቀበት።ሥልጣን፡ላይ፡አምጥቶ፡ያስቀመጠውን፡ኽርማን፡ኮኸን፡አሰብ፡ለኢትዮጵያ፡እንድትሆን፡የነገረውንም፡ቃል፡እንኳ፡አለማክበሩ፡ይነገራል።የአሰብም፡ጉዳይ፡ይዋል፡ይደር፡እንጂ፡ማንም፡ኢትዮጵያዊ፡ዛሬም፡ሆነ፡ወደ፡ፊት፡ችላ፡ብሎ፡የማይመለከተው፡መሆኑን፡አመፀኛው፡አረመኔ፡ለገሠ፡ዜናዊ፡እንደሚያወራው፡ተንጥልጥሎ፡አይቀርም።እናም፣ነፍስ፡ገዳዩ፡አመፀኛ፡ለገሠ፡ዜናዊና፡እሱን፡የመሰሉት፡ከሃዲዎች፡ሲወገዱ፣አሰብ፡ከእናት፡አገሯ፡ጋር፡ትዋሃዳለች።ከወገኖቻችንም፡ጋራ፡ተወያይተን፡አብረን፡እንኖራለን፡ብለን፡እናምናለን።ከዚህ፡ሌላ፡የፋሽስቱ፡ለገሠ፡ዜናዊ፡አስተዳደር፡ያደረገውና፡የሚያደርገው፡በደል፡ቢኖር፡የአገሩን፡ገበሬ፡ነቅሎ፡ለቻይና፣ለሕንድ፣ለእሩቅ፡ምሥራቅ፣ለዓረብና፡...........የማሳሰሉት፡ሀብታሞች፡ለም፡መሬት፡ለእርሱ፡ኪስ፡ማወፈሪያ፡ዘዴ፡እያሰናዳ፡መሸጡ፡የማይገባ፡መሆኑ፡ግልጽ፡ነው።ወደፊትም፡ይቀጥልበታል።በውሸትና፡በማታለያ፡ዘዴው፡ያስባሰባቸው፡ግብስባሶ፡የምክር፡ቤት፡አባሎች፡ይህን፡የመሰለውን፡በደል፡በሕዝብ፡ላይ፡ሲፈጽም፡ከሃዲና፡ለሆዳቸው፡ተገዥ፡በመሆናቸው፡ዝም፡ብለውታል።ከጎንደር፡ግዛት፡ገበሬዎችን፡የእርሻ፡አባርሮ፡ለሱዳን፡መበልጸጊያ፡የሸጠው፡የማይገባ፡ተግባር፡በመሆኑ፡ወደ፡ፊት፡ይጠየቅበታልና፡ይወቀው።የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ዕምነትህ፡በእግዚአብሔር፡ብቻ፡ስለ፡ሆነ፤የፋሽስቱ፡ለገሠ፡ዜናዊ፡አስተዳደር፡ማለቂያው፡ግዜ፡ርጅም፡አይደለም።በቅርቡ፡ፍርዱን፡ያገኛል።ይህ፡ሁልሉ፡በደል፡ሊደርስ፡የቻለውና፡ኢትዮጵያ፡የምትረግመው፡ሰው፡ቢኖር፡መንግሥቱ፡ኃይለማርያምን፡ነው።በሀገር፡ፍቅር፡ደማቸውን፡ያፈሰሱ፡አጥንታቸውን፡የከሰከሱና፡አልለንልሽ፡ኢትዮጵያ።አንበገርም።ይሉ፡የነበሩ፡ልጆቿን፡ባልባሌ፡ሁኔታ፡ጨፍጭፎ፡በባዶ፡ቤት፡ያስቀራት፡በሜዳ፡ላይ፡ሲደነፋ፡የነበረው፡ፈሪ፣ጓደኞቹን፡ለትግሬ፡አመፀኛ፡(ወያኔ)፡ወርሮበሎች፡ትቶ፡በሽሽት፡ካመለጠ፡በኋላ፡በዘንባብዌ፡ተደብቆ፡ይኖራል።እርሱም፡ሆነ፡ፋሽስቱ፡ለገሠ፡ዜናዊና፡ግብረ፡አበሮቹ፡ጭምምር፡እንደሌሎቹ፡ዓለማት፡አረመኔ፡አምባገነኖች፡ድርሻ፡ፍርዳቸውን፡ያገኛሉ።ያለ፡ምክንያት፡የጨፈጨፋት፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ደም፡ይፋረዳቸዋልና፡ግዜያቸውን፡ይጠብቡ።

ኢትዮአጵያ፡በታላቁ፡ጉባኤዋ፡(በሲኖዶሷ)፡ርዕሰ፡ሊቃነ፡ጳጳስ፡በሕይወት፡እያልለ፡ሌላ፡ርዕሰ፡ሊቃነ፡ጳጳስ፡የሾመችበት፡ታሪካዊ፡መዝገብ፡ኑሯት፡አላነበብንም።ገና፡ከጥንስሱ፡የደርግን፡መ

ድዳከም፡ሕዝብ፡በስሚ፡ስሚ፡መድዳረሻውን፡ሲያጠያይቅ፤የትግሬ፡አመፀኞች፡(ወያኔዎች)፡ሰላዮች፡እየተዘዋወሩ፡ቅስቀሳ፡ጀምረው፡ነበረ።እናም፣የትግሬን፡መሬት፡በስድሳ፡ጠበንጃ፡የሸጠው፡የፋሽስት፡አሽከሩ፡ከሃዲ፡ደጃዝማች፡ገብረ፡ሥላሴ፡ልጅ፡ደጃዝማች፡ዘውዴ፡ገብረ፡ሥላሴና፡ተድላ፡ተሾመ፡በመድኃኔ፡ዓለም፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ዋሽንግተን፡ድ.ሲ.ለነጋድራስ፡ጳውሎስ፡ማስተዋዎቂያ፡አዘጋጁ።በሸክላ፡ተዘጋጅቶ፡የተሰራጨውንም፡ተንቀሳቃሽ፡ምሥል፡ዓይተን፡እግዚኦ፡በማለት፡አግባብ፡ያለመሆን፡ቅሬታችንን፡አስታውቀን፡ነበረና፡መልሱን፡አልላኩልንም።በጥናታችን፡እንደ፡ደርረስንበት፣ጳውሎስ፡በ፡፲፱፻፶፱፡ዓመተ፡ምሕረት፡የኢትዮጵያን፡ታሪካዊ፡ባሕል፡ለማስተዋወቅ፡ወደ፡ሞንትሬል፣ካናዳ፡ከተጓዡት፡አንዱ፡ነበረ።ትርዒቱ፡ካልለቀ፡በኋላም፡እዚያው፡ቀርተው፡ትምህርታቸውን፡ከቀጠሉት፡እንደብበረ፡ተረድተናል።ተማሪ፡በነበረበት፡ወቅትም፡ዓለማዊ፡ጨፍፋሪ፡እንደ፡ነበረና፡“ቡጊ”፡በመባል፡ቅጽል፡ስም፡ይታወቅ፡ነበረ፡አሉ።ከፈንሣዊት፡ልጅ፡እንዳስወለደም፡የሚነገርለት፡የዐድዋው፡ጳውሎስ፡ከመሠረቱ፡የትግሬ፡አመፀኞች፡ሰላይና፡ታጋይ፡እንጂ፡መንፈሳዊነት፡እንደ፡ሌለው፡ብዙ፡ማስረጃወች፡አግኝተናል።አዲስ፡አበባ፡ውስጥም፡እንዳያችሁት፡የአመሪካዊቷን፡ዘፋኝ፡ቢያንሴን፡አስኅብኝና፡መጽሐፍ፡ቅድዱስ፡ሸልላሚ፡መሆኑ፤ከወይዘሮ፡እጅጋዬሁ፡ጋራስ፡ያልለው፡ትውውቅ፡የመንፈሳዊ፡አብባትን፡ክብር፡የሚያቆሽሽ፡ሆኖ፡እናየዋለን።በቦሌ፡የተሠርራለትን፡ምሥለ፡ጣዖት፡እንዳይፈርስ፡ሽንጧን፡ገትትራ፡የምትጮህለት፡እጅጋዬሁን፡ምን፡ልትሏት፡ይግገባል?።

ስለዚህ፡የአዲስ፡አበባው፡ጳጳስ፡ነጋድራስ፡ጳውሎስ፡የአመፀኛው፡አረመኔ፡ለገሠ፡ዜናዊ፡አስተዳደር፡ተሿሚ፡በሃይማኖታችን፡የታላቁ፡ጉባኤን፡(የሲኖዶስን)፡ሕግ፡ጥሶ፡የተሾመው፡የሚያደርገው፡ሁልሉ፡መንፈሳዊነት፡የጐደለው፡አጋንታዊና፡ተገቢ፡አለ፡መሆኑን፡የተረዳ፡ይመስለናል።ጳውሎስ፡ለብዙ፡ዘመናት፡ሲወርድ፡ሲዋርረድ፡የቆየውን፡ባሕላችንን፡ምዕመናኑ፡በየቤተ፡ክርስቲያን፡እግዚኦ፡በማለት፡ለፈጣሪያቸው፡የሚያቀርቡትን፡ጸሎት፡የከለከለ፡እንደ፡ቅልልብ፡ድልብ፡በሬ፡ነውና፡የሃይማኖት፡መሪ፡ነኝ፡ብሎ፡ሳይናገር፡ዝምም፡ይበል።ምዕመናኑ፡የሚሰጡትን፡የስዕለት፡ዶላርና፡ዩሮ፡ገንዘብ፡በየቤተ፡ክርስቲያኑ፡የመደባቸው፡ወኪሎቹ፡እየሰበሰቡ፡ወደ፡ግልል፡ሣጥኑ፡እንዲገባ፡ያደርረገ፡መሆኑ፡ይነገራል።ይህ፡እንደሱ፡ካልለ፡የሃይማኖት፡አብባት፡ነኝ፡ባይ፡ይጥጠብበቅ፡ነብበር፡ወይ?።እንዴት፡የእግዚአብሔር፡ተገዥ፡ነኝ፡ሊል፡ይችላል?።አያፍርም?።የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡በረሃብ፡እያልለቀ፡ሳልለ፤አልተራበም፡እያለ፡ለሚናገር፡ውሸታም፡የትግሬ፡አመፀኛ፡(ወያኔ)፡አስተዳደርን፡በመገዝዘት፡ፈንታ፡ዝምም፡ብሎ፡ይምመለከታል።ተድላና፡ደስታን፡መርጦ፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ሲሠቃይ፡እየተመለክከተ፡ዝምም፡ማለቱ፡የዚህ፡ዓለም፡ተገዥ፡እንጂ፡መሥዋዕትን፡የማይቀበል፡ግዙፍ፡ሆዳም፡ሰው፡ነው።እንዴት፡የእነ፡አቡነ፡ጴጥሮስን፡ለሀገራቸው፡መሥዋዕት፡መሆን፡ይስተዋል?።ምናልባትም፡በፋሽስት፡ሙሶሎኒ፡ጦር፡አዛዦች፡ትእዛዝ፡በከሃዲ፡ዘመዶቹ፡የመገደላቸውን፡ታሪክ፡ላለማውሳት፡ፈልጎ፡ይሆን?።የቅርቡን፡አቡነ፡ተክለ፡ሃይማኖትን፡የደርግ፡አገዛዝ፡ያሳዘናቸው፡በመሆኑ፡ከምግብና፡ውሃ፡ተቆጥበው፡እራሳቸውን፡ጐድተው፡ሕይወ ታቸውን፡ያሳለፉትን፡አብባት፡ምሳሌ፡በማድረግ፡ለአንድ፡ቀን፡እንኳ፡እነ፡ፋሽስት፡ለገሠ፡ዜናዊን፡አውግዞ፡መሥዋዕት፡ለመሆን፡አይሞክርም።የእግዚአብሔር፡ፍርድ፡እሩቅ፡ስላልሆነ፡ይጠብብቅ።

የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ሆይ!፤

ቀድሞም፡በወላጆችህ፡ዘመነ፡መንግሥት፡ኢትዮጵያ፡በጥቂት፡ጀግኖች፡እንጂ፡አብሯቸው፡የተሰልለፈው፡ፎካሪና፡ሥውር፡ተቀጥጣሪ፡ሁልሉ፡ከክህደት፡ጋራ፡ሆዱን፡ሞይ፡ሀገሩን፡ወድዳድ፡ሆኖ፡በመግኜቱ፡አልነበረም፤የወራሪ፡ጠላትን፡ቅስም፡ሰብረው፡ድለን፡የተቀዳጁት።አሁንም፡እየተሰቃዬህ፡ያልለኸው፡በነዚያ፡ሥውር፡ተቀጥጣሪ፡ከሃዲ፡ርዝራዦች፡ነው።መንግሥት፡ሲብባልም፡አንተ፡ሕዝቡ፡እንጂ፡አገልጋይ፡አገረ፡ገዦችህ፡አልነብበሩምና፡ዓለማትን፡በሚያስደምም፡ሁኔታ፡

የ፴፰፡ዓመታት፡መከራን፡ችለህ፡ዐዋቂነትህን፡በማስመስከር፡ላይ፡ትገኛለለህ።ሆኖም፣ያ፡ትሑትነትህ፡ተሻሽሎ፡የመንግሥትነት፡ሕግጋዊ፡መብትህን፡በቁጥጥርህ፡ለማስከብበር፡ማሥሰቡ፡ተገቢ፡ይመስለናል።ትናንት፡ወላጆችህ፣ዛሬና፡ነገ፡ደግሞ፡የሚያንቋሸሹብህ፡ታሪክህን፡በጥራት፡አድድሰህ፡ለተነገ፡ወዲያው፡ትውልድድ፡የሚትተላለለፍ፡ዕዳ፡የልለሽ፡ነፃነትህን፡እንደምትቀዳጅ፡ከፍፍ፡ያለ፡እምነታችን፡ነው።

ኢትዮጵያንና፡ሕዝቧን፡እግዚአብሔር፡ባርኮና፡አጠንክሮ፡ይጠብብቅልን።አሜን።

ከዜናማርቆስ፡መርሐ፣ካናዳ።

አስተያየት፡ወይም፡ጥያቄ፡ካልላችሁ፡እለቁጥሩአችንን፡እንሆ!፦ zienamarqos@yahoo.com

## ማስገንዘቢያ፡-

የቃላት፡አጥጠቃቀማችን፡የኢትዮጵያዊነት፡ባሕላዊ፡ትሕትና፡የጐድደለው፡መሳይ፡ጠንካርራ፡እንደ፡ሆነ፡እናውቃልለን።ስለ፡ሆነም፣አንባቢዎቻችን፡የጠላትን፡ሕዝብ፡አስሰቃይነትና፡ሀገር፡ሻጭንነት፡በማጤን፡ከምርሬት፡አንፃር፡ያዝዘጋጅጀነው፡መሆናችንን፡እንዲገነዘቡልልን፡በትሕትና፡እናስገነዝባልለን።